የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 62
ADDIS ABABA 4th September, 2007

**ማ ው ጫ**

አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ… ገጽ ፫ሺ፱፻፲፭

**CONTENTS**

**Proclamation No. 551/2007**

Ethiopia Commodity Exchange Authority Proclamation Page 3915

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱

## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ቀልጣፋና ዘመናዊ የግብርና ምርቶች ግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የምርት ግብይት ሥርዓቱ ፍትሐዊ፣ ግልጽና የተቀላጠፈ መሆኑን ለማረጋገጥና በገበያው የሚሳተፉትንም ሆነ በአጠቃላይ የኅብረተሰቡን ጥቅም ማስጠበቅ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህንንም ለማድረግ ያስችል ዘንድ የምርት ግብይት ሥርዓቱን የሚቆጣጠር የመንግሥት አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO.551/2007.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIA COMMODITY EXCHANGE AUTHORITY

**WHEREAS,** it is found necessary to establish an efficient and modern agricultural commodities marketing system;

**WHEREAS,** it is essential to ensure that the marketing system is fair, transparent and efficient to protect the interests of the different actors of the system and the public at large;

**WHEREAS,** in order to achieve foregoing it has become necessary to establish a government organ entrusted with the responsibility of regulating the proper functioning of a commodity exchange;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopia Commodity Exchange Authority proclamation No. 551/2007."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም" ማለት በምርት ገበያ ወይም በባለሥልጣኑ እውቅና ያገኘ የአገር ውስጥ ባንክ ወይም ተመሳሳይ የፋይናንስ ተቋም ነው፤

፪/ "የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም" ማለት አንድ ድርጅት በአገናኝነት ወይም በአቀራራቢነት የሚሠራበት ሥነ ሥርዓት ሆኖ፣ ድርጅቱ ለግብይቱ አፈጻጸም የገዢና የሻጭን ሚና በመውሰድ በተዋዋይ ወገኖች የሚሰጡትን ትዕዛዞች የሚያስታርቅበትና የገንዘብ ክፍያና ርክክብ የሚፈጸምበት አሠራር ነው፤

፫/ "ምርት" ማለት ከሌላ አንድ ዓይነት ምርት ጋር መለዋወጥ የሚችል ምርት ነው፤

፬/ "የምርት ገበያ" ማለት ወጥ ሆነው በተዘጋጁ ምርት ነክ ውሎች ግብይት የሚፈጸምበት የምርት ገበያ ነው፤

፭/ "ውል" ማለት ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን መጠን፣ ዋጋ፣ ደረጃ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበትና የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያካትት ስምምነት ነው፤

፮/ "አስቸኳይ ሁኔታ" ማለት የተለመዱትን የገበያ ተግባራት የሚከለክል ማናቸውም ከፍተኛ የሆነ የገበያ ቀውስ ነው፣

፯/ "የግብይት ፈጻሚ" ማለት ለሌሎች ወይም ለራሱ ሲል የምርት ግብይት ውሎችን በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ የተሠማራ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤

፰/ "የውስጥ አዋቂ ንግድ" ማለት የተጣለበትን ከፍተኛ እምነት ወይም አደራ ውይም በእምነት ወይም በአመኔታ ላይ የተመሠረተን ሌላ ግንኙነት በማፍረስ ለሕዝብ ያልተገለጸ መረጃን በመጠቀም የምርት ግብይት ውልን መግዛት ወይም መሸጥ ነው፤

፱/ "አሳሳች ድርጊት" ማለት የምርትን ዋጋ ወይም መጠን በተመለከተ የገበያ ተሳታፊዎችን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማናቸውም ድርጊት ነው፤

## 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "clearing institution" means the Ethiopia Commodity Exchange or domestic bank or similar financial institution recognized by the Authority;

2/ "clearing and settlement" means the procedure by which an organization acts as an intermediary and assumes the role of a buyer and seller for Exchange traded transactions in order to reconcile orders between transacting parties, and insures the physical or financial settlement of the transaction;

3/ "commodity" means a product which is interchangeable with another product of the same kind;

4/ "commodity exchange" means an exchange where standardized commodity-linked contracts are traded;

5/ "contract" means a standardized agreement to buy or sell a specified commodity, detailing the amount, grade and price of the commodity and the date on which the contact will mature and become deliverable for purposes of trading on the Exchange;

6/ "emergency" means any major market disturbance, which prevents the normal functioning of the market;

7/ "exchange actor" means any person recognized by the Authority who engages in the business of buying and selling Exchange traded contracts for others or for his own account.

8/ "insider trading" means buying or selling an Exchange traded contract using nonpublic information, in breach of a fiduciary duty or other relationship of trust and confidence.

9/ "manipulation" means any conduct likely to mislead or deceive market participants concerning the value and/or trading volume of a commodity.

፲/ "የመያዣያ ገንዘብ" ማለት ግ™ ፈጻሚዎች በገበያ ላይ ለሚፈጸሙት አንድ ግብይት በመያዣነት ሊያስቀምጡት የሚገባ ገንዘብ ነው፤

፲፩/ "አባል" ማለት ለምርት ገበያ የሚጠይቀውን የአባልነት መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

## ክፍል ሁለት
## የምርት ገበያ ባለሥልጣን

### ፫ መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን /ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

### ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ይኖሩታል።

### ፭. ዓላማዎች

የባለሥልጣኑ አጠቃላይ ዓላማ ውጤታማ የሆነ ዘመናዊ የመገበያያ ሥርዓት መገንባቱን ማረጋገጥ፣ የምርት ገበያው አስተማማኝ፣ ግልፅና የተረጋጋ አሠራር እንዲኖረው መቆጣጠር፣ እንዲሁም የሻጮችን፣ የገዢዎችን፣ የአገናኞችንና በአጠቃላይ የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ሆኖ ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

፩/ በኃላፊነት የሚከናወኑ የፈጠራ ሥራዎችን ማበረታታት፣ ሁሉም የገበያ ተሳታፊዎች የገበያ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ወይም በገበያዎችና በገበያ ተሳታፊዎች መካከል የሚደረጉ ተገቢ ውድድሮችን ማዳበር፤

፪/ ዋጋን በተመለከተ አሳሳች ድርጊትን ወይም ሌላ የገበያውን ህልውና የሚያናጋ ድርጊትን መግታትና መከላከል፣

፫/ ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ የግብይቶችን የፋይናንስ አቋም የመጠበቅና አጠቃላይ የገበያ ሥርዓቱን የሚያናጉ አደጋዎች እንዳይከሰቱ መከላከል፤

10/ "margin" means the funds, which must be deposited by Exchange Actors as collateral for a given transaction on a Commodity Exchange.

11/ "member" means any person that fulfills the requirements of a Commodity Exchange.

12/ "person " means any physical or juridical person.

## PART TWO
## THE ETHIOPIA COMMODITY EXCHANGE

### 3. Establishment

1/ The Ethiopia Commodity Exchange Authority (hereinafter "Authority") is hereby established as an autonomous public institution of the Federal Government.

2/ The Authority shall be accountable to the prime Minister.

### 4. Head Office

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as necessary.

### 5. Objectives

The general objective of the Authority shall be to ensure the development of an efficient modern trading system, and to regulate and control the secure, transparent and stable functioning of a Commodity Exchange and to protect the rights and benefits of sellers, buyers, intermediaries and the general public. Its specific objectives are to:

1/ promote responsible innovation, access to market information by all market participants and fair competition among markets and market participants;

2/ deter and prevent price manipulation or any other disruption of market integrity;

3/ ensure the financial integrity of all transactions subject to this proclamation and the avoidance of systemic risk; and

፬/ የገበያ ተሳታፊዎችን ከመታለልና ተገቢ ካልሆኑ ሌሎች ድርጊቶች እንዲሁም የደንበኞች ንብረት አለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ መጠበቅ።

## ፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ለክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ዕውቅና የመስጠት ወይም የመንሳት፤

፪/ ለግብይት ፈጻሚዎች ዕውቅና የመስጠት ወይም የመንሳት፤

፫/ የምርት ገበያን፣ የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማትንና የግብይት ፈጻሚዎችን ቁጥጥር በተመለከተ መመሪያዎችን የማውጣት እንዲሁም ይህንኑ በተመለከተ የምርመራ፣ የማፅደቅና ትክክለኛነቱን የማረጋገጥ ሥልጣኑን ተግባራዊ የማድረግ፤

፬/ ከምርት ገበያ ሥራ ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት አማካሪዎችን፣ የአማካሪ ድርጅቶችን፣ የሕግ ባለሙያዎችን፣ የሂሣብ አዋቂ ባለሙያዎችን አሠራር የመቆጣጠር፤

፭/ የምርት ግብይት ውሎችን ዝርዝር ይዘት፣ ሽያጭና ግዢ መርሆዎች በሚመለከት መመሪያ የማውጣት፤

፮/ የምርት ግብይት ውሎች ክፍያንና ርክክብ አፈጻጸምን የመቆጣጠር፣

፯/ ከምርት ግብይት ጋር በተያያዘ የውስጥ አዋቂ ንግድን፣ ማታለልንና ተገቢ ያልሆነ የንግድ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን የመውሰድ፤

፰/ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር ጋር በመተባበር የምርት ግብይትን በተመለከተ የገለልተኛ የኦዲት አሠራር መርሆዎችን የመወሰን፤

፱/ በዚህ አዋጅ መሠረት በእጁ የገቡትን ወይም የቀረቡለትን የሂሣብ መግለጫዎች፣ ሪፖርቶችና ሌሎች ሰነዶች የመመርመር፣ ከምርት ገበያው፣ ከክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት፣ ከግብይት ፈጻሚዎች፣ ከውስጥና ከውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት እንዲቀርብለት የመጠየቅ፤

፲/ ከምርት ገበያና ከገበያ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የሚፈጸሙ የሕግ መጣስ ድርጊቶችን የመመርመርና እርምጃ የመውሰድ፤

4/ protect all market participants from fraudulent or other abusive trading practices and misuse of customer assets;

## 6. Powers and Duties of the Authority

The authority shall have the powers and duties to:

1/ grant or withdraw recognition of any Clearing Institutions:

2/ grant or withdraw recognition of any Exchange Actors;

3/ formulate directives concerning regulation of a Commodity Exchange, Clearing Institutions and Exchange Actors and to exercise its power of examination and approval or verification of the same;

4/ regulate the conduct of investment advisors, consulting companies, law practices, accounting professionals, as it relates to a Commodity Exchange's businees;

5/ issue directives on the specifications, sale and purchase principles of any Exchange traded contracts;

6/ regulate the clearing and settlement of Exchange trade contracts;

7/ take appropriate measure to prevent insider trading, fraudulent and unfair trade practices relating to Exchange traded contracts;

8/ determine the principles related to independent auditing operations as they relate to Exchange transaction, in consultation with the Federal Auditor General;

9/ inspect financial statements, reports and other documents it obtained or submitted to it in accordance with provisions of this proclamation, to request reports from a commodity Exchange, clearing Institutions, Exchange Actors, and internal and independent auditors;

10/ investigate and act upon violations of laws concerning the regulation of a Commodity Exchange and related businesses;

፲፩/ የምርት ገቢያን ሠራተኞች በሚመለከት ስለሚደረግ ቁጥጥር እንዲሁም ከመብትና ግዴታቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ደንቦችንና መርሆዎችን በተመለከተ መመሪያ የማውጣት፤

፲፪/ የምርት ገቢያን የክርክር አፈታት መመሪያና ሥርዓት ያጸድቃል፤

፲፫/ የምርት ገቢያ ቁጥጥርን እንዲሁም የግብይት ፈጻሚዎችን፣ የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማትን፣ የግብይት ፈጻሚዎች ማህበርን ዕውቅናንና ቁጥጥርን በተመለከተ በባለሥልጣኑ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ክፍያዎች የማስከፈል፤

፲፬/ ከምርት ገቢያ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በተመለከተ ለሕዝብ የሚሰጠውን ትምህርት የማሳደግ፤

፲፭/ አግባብ ካላቸው የመንግሥትና የግል አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት የመፍጠርና የመተባበር።

## ፯. የመዳኘት ሥልጣንና ጉዳዮችን ስለመምራት

፩/ ባለሥልጣኑ በሥልጣን ክልሉ ውስጥ የሚወድቁ ጉዳዮችን በሚዳኝበት ጊዜ፦

ሀ/ ማንኛውንም ሰው የመጥራትና በጥሪው መሠረት እንዲገኝ የማድረግ፣ ቃለ መሐላ በማስፈጸም ምርመራ የማካሄድ፣

ለ/ ማናቸውም ሰነድ እንዲፈለግና እንዲቀርብ የመጠየቅ፣

ሐ/ በቃለ መሐላ የተረጋገጠ ማስረጃ የመቀበል፣

መ/ የሕዝብ ወይም የመንግሥት ሰነድ ወይም ኮፒውን ከማናቸውም መሥሪያ ቤት እንዲቀርብለት የመጠየቅ፣ እና

ሠ/ አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ ሥልጣን ይኖረዋል።

፪/ ከምርት ገቢያ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ወንጀል ሲያጋጥመው ጉዳዩን ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ማስተላለፍ አለበት።

፫/ ምርመራ እንዲካሄድ ካደረገ በኋላ ማናቸውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ከተገኘ ወይም ሊጥስ የሚችል መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የተባለው ሰው ድርጊቱን ከመፈጸም እንዲገታ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

11/ issue directives on the rules and principles relating to supervisions, rights and duties of those who shall be employed at a Commodity Exchange;

12/ approve the dispute settlement rules and procedures of a Commodity Exchange;

13/ levy fees and charges related to the regulation of a Commodity Exchange and recognition and regulation of Exchange Actors, Clearing Institutions and Exchange Actors Associations, as prescribed by its directive;

14/ promote public education regarding a Commodity Exchange and related businesses; and

15/ liaise and collaborate with appropriate public and private bodies.

## 7. Adjudication and Referral of Cases

1/ The Authority shall, in adjudicating cases falling under its jurisdiction, have the power to:

a) summon and enforce the attendance of any person and examine him under oath;

b) require the discovery and production of any document;

c) receive evidence on affidavits;

d) requisition any public record or copy thereof from any office; and

e) take administrative sanctions;

2/ When any criminal offence related to the operation of a Commodity Exchange comes before the Authority, the Authority shall forward the case to the appropriate judicial body.

3/ If the Authority finds, after causing an inquiry to be made, that any person has violated, or is likely to violate any provisions of this Proclamation or any directives made hereunder, the Authority may pass an order enjoining such person from committing such violations.

**፰. ስለባለሥልጣኑ አቋም**

ባለሥልጣኑ፣

፩/ የምርት ገበያ ቦርድ /ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ/፣

፪/ በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና፣

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣
ይኖሩታል።

**፱. የቦርድ አባላት**

፩/ ቦርዱ የሚከተሉትን ይይዛል፣

ሀ/ አንድ ሊቀመንበር፣

ለ/ ከግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር የሚመደብ አንድ አባል

ሐ/ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚመደብ አንድ አባል፣

መ/ ከንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚመደብ አንድ አባል፣ እና

ሠ/ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚመደብ አንድ አባል።

፪/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በአባልነት ይሳተፋል።

፫/ የቦርዱ ሊቀመንበርና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከቱት አባላት በመንግሥት ይሾማሉ።

፬/ የባለሥልጣኑ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ ካልፈቀደ በቀር ማንኛውም የቦርድ አባል ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ሥራውን ከለቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በግብይት ሥራ ላይ ከተሰማራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የሥራ ቅጥር መቀበል ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ በማናቸውም ሥራ መሰማራት አይችልም።

**፲. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ለባለሥልጣኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል።

**8. Organization of the Authority**

The Authority shall have:

1/ an Exchange Authority Board (hereinafter the "Board");

2/ a Director General to be appointed by the Government; and

3/ the necessary staff.

**9. Members of the Board**

1/ The Board shall constitute:

a) a Chairperson

b) a Board member from the Ministry of Agriculture and Rural Development:

c) a board member from the Ministry of Finance and Economic Development;

d) a Board member from the Ministry of Trade and Industry; and

e) a Board member from the National Bank of Ethiopia.

2/ The Director General of the Authority shall participate in the meetings of the Board with a status of a member.

3/ The Chairperson and members of the Board referred to in sub-article (1) of this Article shall be appointed by the Government.

4/ Board members or the Director General, for a period of three years from the date on which they cease to hold office, except with the previous approval of the Authority, shall not conduct any business related to or accept any employment with any person or entity dealing with transactions subject to directives by the Authority.

**10. Power and Duties of the Board**

1/ The Board shall exercise the powers and duties of she Authority specified under Article 6 of this Proclamation

፪/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ ፖሊሲ የመቅረጽና የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት የመምራት ሥልጣን ይኖረዋል።

## ፲፩. ስለቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

፩/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ ለቦርዱ የሚቀርብ ማናቸውም ጉዳይ ቦርዱ በአብላጫ ድምፅ ይወስናል፣ ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የቧርዱ ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ስብሰባውን የመራው የቦርድ አባል ሁለተኛ ወይም ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፪/ በባለሥልጣኑ መመሪያዎች በተመለከቱት መሠረት ቦርዱ በሳምንት አንድ ጊዜ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ሲጠየቅ ይሰበሰባል፣ የስብሰባ ምልዐተ ጉባዔን ጨምሮ በቦርዱ ስብሰባ ስለሚከናወኑ ሥራዎች በልምድ ተቀባይነት ያገኙ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንቦችን ያከብራሉ።

፫/ የቦርዱ ሊቀመንበር በማናቸውም ምክንያት በቦርዱ ስብሰባ መገኘት ያልቻለ እንደሆነ፣ በሰብሳቢው የተወከለ ሌላ ማንኛውም የቦርድ አባል ስብሰባውን በሰብሳቢነት ይመራል።

## ፲፪. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የባለሥልጣኑ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ በተለይም

ሀ/ የግብይት ተሳታፊዎችና የክፍያ አፈጻጸም ክትትል፣

ለ/ የገበያ ክትትል፣

ሐ/ የሕግ አፈጻጸም ክትትል፣

መ/ የኢኮኖሚ ትንተና፣ሥራዎችን በበላይነት የመከታተል ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጐች መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳ ድራል፣

2/ The Board shall have the power to formulate policy related to the powers and duties of the Authority as prescribed under this proclamation and oversee the functions of the Authority

## 11. Procedures of the Meeting of the Board

1/ All issues related to the function of the Authority as prescribed under this Proclamation that come before the Authority shall be decided by a majority of votes to members of the Board and in the event to equality of votes, the Chairperson of the board or in his absence, a board member designated by the Chairperson shall have a second or casting vote.

2/ The board shall meet weekly, or as the Director General so requests, and shall observe customary rules of procedure with regard to the transaction of business at its meetings including quorum as may be provided by directives.

3/ If for any reason, the Chairperson is unable to attend the meeting of the Board, any other Board member designated by the Chairperson shall preside at the meeting.

## 12. Power and Duties of Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority and shall direct and administer the operational activities of the Authority, including but not limited to:

a) Exchange Actors and Clearing Oversight;

b) Market Surveillance and Oversight;

c) Enforcement; and

d) Economic Analysis.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) employ and administer the employees of the Authority, in accordance with federal civil service laws;

ለ/ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ያስፈጽማል፣

ሐ/ በፀደቀው የባለሥልጣኑ በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

መ/ ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፣

ሠ/ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት ያቀርባል።

## ፲፫. <u>የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር በውክልና ስለመስጠት</u>

፩/ በአንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/፣ /፫/፣ /፭/፣ /፲፩/ እና /፲፪/ ከተመለከቱት በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት፣

ሀ/ በባለሥልጣኑ ለተቋቋመ ማናቸውም ኮሚቴ፣ ወይም

ለ/ ለምርት ገበያ፣

በውክልና መስጠት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠ ውክልና የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት ጐን ለጐን ተግባራዊ ማድረግን አይከለክልም።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት አለበት።

## ፲፬. <u>በ ጀ ት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፲፭. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክላቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

b) prepare the annual work program and budget of the Authority, and implement same, upon approval by the Board;

c) effect expenditure in accordance with the budget approved for the Authority;

d) represent the Authority in all its dealings with third parties; and

e) submit reports on the activities of the Authority.

## 13. <u>Delegation of Powers and Duties of the Authority</u>

1/ The Authority may delegate any of its powers or duties under this Proclamation, except the powers and duties described under sub-articles 1, 3, 5, 11 and 12 of Article 6, to:

a) any committee established by the Authority; or

b) a Commodity Exchange.

2/ A delegation under this Article shall not prevent the concurrent performance or exercise of the powers and duties of Authority.

3/ Notwithstanding Sub-Article (1) and (2) of this Article, the Authority is responsible for the carrying out of its powers and duties under this proclamation.

## 14. Budget

The budget of the Authority shall be allocated by the Government.

## 15. Books and Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The Authority's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General or by Auditors designated by him.

## ክፍል ሦስት
## ለግብይት ፈጻሚዎች ዕውቅና ስለመስጠት

### ፲፮. እውቅና የማግኘት አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ እውቅና ካላገኘ በቀር፣ በምርት ገበያ ወይም በምርት ገበያ ላይ ደንቦች ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ማናቸውንም የምርት ግብይት ውል በግብይት ፈጻሚነት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ፣ ትዕዛዞችን ለማፈላለግ ወይም ለመቀበል አይችልም።

፪/ በግብይት ፈጻሚነት እውቅና ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርበታል። ማመልከቻው በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት በተዘጋጀው ቅጽና የአቀራረብ ሥርዓት መሠረት ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን መረጃዎችና ፍሬ ነገሮች አካቶ መቅረብ ይኖርበታል። ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተገቢ የመሰለውን የእውቅናና የእውቅና ዕድሳት ክፍያዎች ይወስናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል።

### ፲፯. እውቅና ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

ማንኛውም ለእውቅና የሚያመለክት ሰው፣

፩/ የተሰማራበትን የንግድ ሥራ ለማከናወን አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ፈቃድ ያለው፣

፪/ በባለሥልጣኑ መመሪያዎች የተወሰነውን አነስተኛውን የካፒታል መጠን የሚያሟላ፣

፫/ በባለሥልጣኑ መመሪያዎች የተመለከተውን አነስተኛውን የትምህርት ወይም የንግድ ብቃት መመዘኛዎችን የሚያሟላ፣

፬/ የሚሳተፍበትን የንግድ ዘርፍ የሚመለከቱ መረጃዎች ማቅረብ የሚችል፣

፭/ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሥራ አስኪያጆች ስሞችንና አድራሻ ዎቻቸውን እንዲሁም የሽርክና ድርጅት ከሆነ የኃላፊዎቹንና የሽሪኮቹን ስሞች፣ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የአክሲዮን ማኅበር ከሆነ የኃላፊዎቹን፣ የዳይሬክተሮቹንና የባለአክሲዮኖቹን ስሞች መግለጽ፣

፮/ በሚገባ የተደራጀ የንግድና የአደጋ ቁጥጥር አመራር ሥርዓት ያለው፣ እና

፯/ በባለሥልጣኑ መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆን፣

አለበት።

## PART THREE
## RECOGNITION OF EXCHANGE ACTORS

### 16. Recognition

1/ It shall be unlawful for any person to engage as an Exchange Actor in soliciting orders or accepting orders for the purchase or sale of any Exchange traded contracts, on or subject to the rules of a Commodity Exchange, unless recognized by the Authority.

2/ Any person desiring to be recognized as an Exchange Actor shall submit an application to the Authority. The application shall be made in such form and manner as prescribed by the authority' directives, giving such information and facts, as the Authority may deem necessary. The Authority shall fix and establish from time to time reasonable fees and charges for recognition and renewal thereof.

### 17. Requirements for Recognition

Any person desiring to be recognized as an Exchange Actor shall

1/ have a business license obtained from the appropriate body with respect to the activities he is engaged in;

2/ fulfill the minimum financial requirement prescribed by the Authority's directives;

3/ have the minimum educational or business qualification prescribed by the Authority's directives;

4/ provide information concerning the business in which he is engaged;

5/ submit the names and addresses of managers of all branch offices, and the names of such officers and partners, if a partnership, and of such officers, directors, and shareholders, if a private limited or share company, as the Authority may direct;

6/ have a well established business and risk management system; and

7/ fulfill other requirements stipulated by directives of the Authority

## ፲፰. ሪፖርት ስለማቅረብና መረጃ ስለመስጠት

እውቅና የተሰጠው የግብይት ፈጻሚ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፯ የተመለከቱትንና በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ ሌሎች ከሥራው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በተመለከተ በየጊዜው ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

## ፲፱. የግብይት ፈጻሚዎችን ዕውቅና ስለማንሳት

፩/ ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና የባለሥልጣኑን መመሪያዎች በግብይት ፈጻሚው መጣሱን በማሳየት ከ፩፻፹ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ዕውቅናውን የማገድ ወይም የመሰረዝ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የእገዳ ወይም የሥረዛ ውሳኔ የሚሰጠው ለግብይት ፈጻሚው ማስታወቂያ ደርሶት እንዲሰማ ከተደረገ በኋላ ብቻ ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ የተወሰነበት ሰው ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካላቀረበ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት በተሰጠ የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቀረበ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ባለሥልጣኑ የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔውን ካላነሳ የግብይት ፈጻሚው በምርት ግብይት ላይ መሳተፍ አይችልም።

# ክፍል አራት
# ለግብይት ፈጻሚዎች ማህበር ዕውቅና ስለመስጠት

## ፳. እ ው ቅ ና

የአባላትን ታማኝነት፣ ሙያዊ ብቃትና የችሎታ ደረጃ ለመጠበቅ ሲባል የግብይት ፈጻሚዎች ማህበር በባለሥልጣኑ ዘንድ በመመዝገብ በግብይት ፈጻሚዎች ማህበርነት ዕውቅና ሊያገኝ ይችላል።

## ፳፩. የምዝገባ መግለጫ

በባለሥልጣኑ ለመመዝገብ የሚፈልግ ማናቸውም የግብይት ፈጻሚዎች ማህበር በባለሥልጣኑ በተዘ ጋጀው ቅጽ መሠረት የምዝገባ መግለጫው እንዲመ ረመርና እንዲፀድቅ ከዚህ በታች ከተመለከቱት መረጃዎችና ሰነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ ማመልከ ቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፣

## 18. Submission of Report and Furnishing of Information

A person who has been recognized as an Exchange Actor shall continue to report and furnish to the authority the information specified under Article 17 of this proclamation and such other information pertaining to his business as the Authority may require.

## 19. Power to Suspend or withdraw Recognition of an Exchange Actor

1/ The Authority is authorized to suspend for a period not to exceed 180 days or to revoke the recognition of any Exchange Actor on a showing that such Exchange Actor has violated any provisions of this Proclamation or the directives of the Authority.

2/ Suspension or revocation under Sub Article (1) of this Article shall only be after a notice to such Exchange Actor and upon a hearing on the record.

3/ Suspension or revocation under Sub Article (1) of this Article shall be final and conclusive, unless within 30 days after such suspension or revocation by the Authority such person appeals to the Federal High Court.

4/ Any notice of suspension or revocation issued under Sub Article (2) of this Article shall remain in effect and bars the Exchange Actor from engaging in Exchange transactions until the matter is decided by the Federal High Court or terminated by the Authority.

# PART FOUR
# RECOGNITION OF EXCHANGE ACTORS ASSOCIATION

## 20. Recognition

Any association of Exchange Actors may be recognized by the Authority as an Exchange Actors Association for the purpose of upholding and maintaining the standards of integrity, professionalism, and skills of its members.

## 21. Registration Statement

Any association desiring recognition by the Authority shall file with the Authority for review and approval,, a registration statement, in such form as the Authority may prescribe setting forth the information and accompanied by the documents specified below:

፩/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመተዳደሪያ ደንቡንና የመመሥረቻ ጽሑፉን ኮፒዎች ማሻሻያ ካለ ከነማሻሻያው፣ ከውስጥ ደንቦቹና ከነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች፤

፪/ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ወይም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ፣ ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚጠይቃቸው ስለማኅበሩ፣ ስለአባላቱ፣ ስለስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንቡና ስለሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች መረጃ፤

፫/ የሥልጠና ደረጃዎችና የብቃት ችሎታ ፈተና መመዘኛ፣

፬/ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ለማስከበር የተዘረጉ የኦዲትና የማስፈጸሚያ ፕሮግራም፣

ሀ/ አባላቱ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ አነስተኛ ካፒታልና የተለያዩ ሂሣቦች አያያዝና ፋይናንስን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች፣ እና

ለ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በአባላቱና ከነርሱ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች ሰዎች የንግድ ሥራዎች አካሄድ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ አነስተኛ ደረጃዎች።

## ፳፪. ስለሪፖርት

በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ የግብይት ፈጻሚዎች በባለሥልጣኑ ሲጠየቁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ የተመለከቱትንና ሌሎች መረጃዎች ለባለሥልጣኑ በቀጣይነት ሪፖርት ማድረግና ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

## ፳፫. ዕውቅናን ስለመከልከል፣ ስለማገድና ስለመንፈግ

ባለሥልጣኑ በማስታወቂያ ጠርቶ የመስማት ዕድል ከሰጠ በኋላ፣ የግብይት ፈጻሚዎች ማኅበር ደንቦች ከባለሥልጣኑ መመሪያዎች ጋር የማይጣጣሙ ሆነው ከተገኙ ማኅበሩን የዕውቅና ምዝገባ ለመከልከል፣ ለማገድ ወይም ለማንሳት ይችላል።

## ክፍል አምስት
## ለክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ዕውቅና ስለመስጠት

## ፳፬. ስለአሠራሩ

፩/ በምርት ገበያ በየቀኑ ከሚካሄድ የምርት ግብይት ውሎች ግዢዎችና ሽያጮች መጠን ጋር ፫ሺ፱፻፳፮ ነማማ የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ አሠራር .ሁም ከምርት ግብይቱ ጋር በተያያዘ የገንዘቦች መተላለፊያ ዘዴዎች ይኖሩታል።

1/ copies of its Articles and Memorandum of association under the relevant provisions of the Civil code, with all amendments thereto, and of its by-laws, and of any rules or instruments corresponding to thereto;

2/ data as to its organization, membership, and rules of procedure, and such other information as the Authority may by directives require as necessary or appropriate in the public interest;

3/ training standards and proficiency testing; and

4/ a program to audit and enforce compliance with the following standards:

a) minimum capital, segregation of accounts, and other financial requirements applicable to its members, and

b) minimum standards governing the trading practices of its members and persons associate therewith for transactions subject to the provisions of this Proclamation.

## 22. Report

Such Exchange Actors Associations, when registered hereunder, shall likewise continue to report and furnish to the Authority the information required under Article 21 of this Proclamation and such other information pertaining to such Exchange Actors Association as the Authority may require.

## 23. Denial, suspension or withdrawal of recognition

The Authority may, after notice and opportunity for hearing, deny, suspend, or withdraw the registration of any Exchange Actors Association if it finds that the rules thereof do not conform to the requirements of the Authority.

## PART FIVE
## RECOGNITION OF CLEARING INSTITUTIONS

## 24. Clearing and Settlement Function

1/ A commodity Exchange shall have a Clearing and Settlement function which will provide matching of all purchases and sales of Exchange traded contracts on a daily basis and a mechanism for the transfer of funds related to Exchange transactions.

፪/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ዕውቅና ሳያገኝ በግብይት ክፍያና ርክክብ ማስፈጸም ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

## ፳፭. <u>ዕውቅና ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች</u>

በክፍያ መፈጸሚያ ተቋምነት ዕውቅና ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው ማመልከቻ በባለሥልጣኑ መመሪያ የተመለከቱትን መረጃዎች መያዝና በተለይም አመልካቹ፣ የሚከተሉትን ማሳየት ይኖርበታል፣

፩/ የተሟላ የፋይናንስ፣ የሥራ እንቅስቃሴና የሥራ አመራርና ሀብቶች ያሉት መሆኑን፣

፪/ ኃላፊነቱን በሚወጣበት ጊዜ የሚያጋጥሙትን ችግሮች አግባብነት ያላቸውን ዘዴዎችንና ሥርዓቶችን በመጠቀም የመቋቋም ችሎታ ያለው መሆኑን

፫/ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በመሆን ክፍያን በተፈለገው ጊዜ በተሟላ ሁኔታ የማጠናቀቅ ችሎታ ያለው መሆኑን፣

፬/ የሚፈጽማቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ከእያንዳንዱ ግብይት ጋር በተያያዘ ስለገንዘብ ፍሰት የተሟላ መረጃ የመያዝ ችሎታ ያለው መሆኑን፣

፭/ ከሌሎች የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ጋር ባለው ግንኙነት ስለማናቸውም የተፈቀዱ ማቻቻያዎች የተመለከቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች የማክበር ችሎታ ያለው መሆኑን፣

፮/ የገንዘብን ወይም የፈንድን ደኅንነት ለመጠበቅና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ደረጃዎችና ሥርዓቶች ያሉት መሆኑን፣

፯/ ግዴታ አለመወጣትን በተመለከተ ውጤታማ፣ ፍትሐዊና ጤናማ አስተዳደር እንዲኖር የሚያግዙ ደንቦችና ሥርዓቶች ያሉት መሆኑን፣

፰/ የምርት ገበያንና የክርክር አፈታት ደንቦች ተግባራዊነትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከታተልና ለማስፈጸም የሚያግዙ የተሟሉ የአሠራር ዘዴዎችና ሀብቶች ያሉት መሆኑን፣

፱/ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ግብአቶችና የአሠራር ሥርዓቶች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውንና የተሟላ አቅምና ዋስትና ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥጥር የሚደረግበትና የሚያጋጥሙ አደጋዎች የሚተነተኑበት ፕሮግራም ያለው መሆኑን፣ እና

2/ It shall be unlawful for any person to engage in Clearing and Settlement of Exchange transaction, unless recognized as a Clearing Institution by the Authority.

## 25. Requirements for Recognition of Clearing Institution

Any person seeking recognition as a Clearing Institution must submit an application to the Authority for this purpose. Every application under this Article shall contain such information as may be prescribed under directives of the Authority, and in particular shall meet requirements relating to:

1/ adequate financial, operational, and managerial resources;

2/ ability to manage the risks associated with discharging the responsibilities of a Clearing institution through the use of appropriate tools and procedures;

3/ ability to complete settlements on a timely basis under varying circumstances;

4/ ability to, maintain an adequate record of the flow of funds associated with each transaction that the applicant clears; and

5/ ability to comply with the terms and conditions of any permitted netting or offset arrangements with other Clearing Institutions;

6/ standards and procedures designed to protect and ensure the safety of funds;

7/ rules and procedures designed to allow for efficient, fair, and safe management of default;

8/ adequate arrangements and resources for the effective monitoring and enforcement of compliance with rules of a Commodity Exchange and for resolution of disputes;

9/ a program of oversight and risk analysis to ensure that the automated systems function properly and have adequate capacity and security; and

፲/ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ አሠራሮች ለአደጋ ሲጋለጡ ተመልሰው የሚቋቋሙበት ቀልጣፋና ፈጣን የአሠራር ሥርዓቶችና ፕላኖች ያሉት መሆኑን፣

ማሳየት አለበት።

## ፳፮. የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማትን ዕውቅና ስለማገድና ስለማንሳት

፩/ ባለሥልጣኑ አንድን የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም አሠራር ደረጃዎችና ሥርዓቶች ከባለ ሥልጣኑ መመሪያ ጋር እንደማይጣጣሙ በማሳየት ዕውቅናውን የመሰረዝ ወይም ከ፩፻፹ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የተሰጠውን ዕውቅና የማገድ ሥልጣን ተሰጥቶታል

፪/ የእገዳና የመሠረዝ እርምጃ የሚወስደው ለተቋሙ ኃላፊዎች በማስታወቂያ እንዲያውቁት ተደርጐ ለባለጉዳዩ የመስማት ዕድል ከተሰጠው በኋላ ይሆናል።

፫/ የእገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፴ ቀናት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ካላቀረበ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል።

## ክፍል ስድስት
## ስለተከለከሉ ግብይቶች እና ስለቅጣት

## ፳፯. ሕገ ወጥ ግብይት

፩/ ማንኛውም ሰው ከግብይት ውል ጋር በተያያዘ፣

ሀ/ ካታለለ፣ ወይም
ለ/ ካጭበረበረ

ድርጅት ከሆነ ከብር ፶ሺ. በማያንስና ከብር ፩ሺ. በማይበልጥ፣ ግለሰብ ከሆነ ከብር ፲ሺ. በማያንስና ከብር ፪፻ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይ በልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፪/ ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ ከግብይት ውል ጋር በተያያዘ አሳሳች ድርጊት ከፈጸመ፣

ለ/ የዕቃ ዋጋን እንደተፈለገ ለመወሰን ይቻል ዘንድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ምርትን ወይም የምርት ግበይት ውሎችን ለመያዝ ወይም ለማከማቸት ቢሞከር፣

10/ emergency procedures and a plan for disaster recovery of automated systems.

## 26. Powers to suspend or withdraw recognition of a Clearing Institution

1/ The Authority is authorized to suspend for a period not to exceed 180 days or to revoke the recognition of any Clearing Institution on a showing that the operation, and procedures of the Clearing Institution do not conform to the requirements of the Authority.

2/ Such suspension or revocation shall only be after a notice to the officers of the Clearing Institution affected and upon a hearing on the record;

3/ Such suspension or revocation shall be final and conclusive, unless within 30 days after such suspension or revocation by the Authority such person appeals to the Federal High Court.

## PART SIX
## PROHIBITED TRANSACTIONS AND PENALTIES

## 27. Unlawful Exchange Transactions

1/ Any person who commits:

a) fraud, or'
b) deceit,

relating to Exchange trade contracts shall be punishable by a fine of at least Birr 50,000 and not more than Birr 1,000,000, or at least Birr 10,000 and not more than Birr 200,000 in the case of a physical person who is an individual, or imprisonment for not more than five years, or both:

2/ Any person who:

a) commits manipulation of Exchange traded contracts;

b) directly or indirectly attempts to hold a given quantity of commodities or Exchange traded contracts for the purpose of manipulating its price;

ሐ/ በመካሄድ ላይ ላለ ንግድ የሌለውን ገፅታ በመስጠት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ምርት ወይም የምርት ግብይት ውሎች ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም የገበያን ሁኔታ ወይም የማናቸውም የምርት ግብይት ውሎችን ዋጋ በተመለከተ አሳሳች መረጃ ከሰጠ፣

መ/ የግብይቱ አፈጻጸም በባለቤትነት ላይ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እየታወቀ ወይም ይኸው ታውቆ ወደ አፈጻጸም እንዲገባ ካደረገ፣ የምርት ግብይት ውሎች እንዲገዙ ወይም እንዲሸጡ ትዕዛዝ ከሰጠ፣

ሠ/ በምርት ገበያ ውስጥና ውጪ ከሚከሰቱ የዋጋ ውጣ ውረዶች ለመጠቀም በማሰብ ስለገበያ ሁኔታ እውነት ያልሆነ፣ አሳሳች መግለጫ ወይም መረጃ ካሰራጨ ወይም ሌላ ሰው እንዲያሰራጭ ካደረገ፣ ወይም

ረ/ ለሌላ ወገን አሳሳች መግለጫ በመስጠትና ውሉ አትራፊ እንደሆነ አስመስሎ በማቅረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የምርት ግብይት ውል እንዲያደርግ ከገፋፋ፣ ድርጅት ከሆነ ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፩ ሚሊዮን በማይበልጥ፣ ግለሰብ ከሆነ ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፪፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ ለሚወስነው ጊዜ ዕውቅናው ይታገዳል ወይም ዕውቅና ወይም ዳግም ዕውቅና ይከለከላል።

## ፳፰. ውስጥ አዋቂ ነጋዴ

፩/ ማንኛውም የባለሥልጣኑ ቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም ተወካይ ይህ አዋጅ በሚመለከተው የምርት ገበያ ውስጥም ሆነ ውጭ ወይም በማናቸውም ተመሳሳይ ንግድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከተሳተፈ ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

c) directly or indirectly purchases or sells commodities or Exchange traded contracts to cause the false appearance of active trading or cause the creation of misleading information regarding the condition of market or price of any Exchange traded contracts;

d) issues an order for the purchase or sale of Exchange traded contracts, the execution of which would involve no change in ownership, or the execution of such an order with knowledge of its character;

e) makes, disseminates or orders someone else to make or disseminate untruthful or misleading statements or information relating to market conditions, with the purpose of benefiting from price fluctuations so created on or off a Commodity Exchange; or

f) directly or indirectly influences another party to enter into an Exchange traded contract by using misleading statements and misrepresenting to such party the profit potential of such contract;

shall be punishable by a fine of at least Birr 50,000 and not more the Birr 1,000,000 or at least Birr 10,000 and not more than Birr 200,000 in the case of a physical person who is an individual, and imprisonment for not more than five years.

3/ Any person convicted of a criminal offense under this Part shall be suspended from recognition and shall be denied recognition or re-recognition for a period as the Authority may determine.

## 28. Insider Trading

1/ It shall be a criminal offense punishable by a fine of at least Birr 20,000 and not more than Birr 100,000 and imprisonment for not more than five years for any Exchange Authority Board member or any employee or agent thereof, to participate, directly or indirectly, in any transaction on a Commodity Exchange or off-Exchange markets, or any trading of the character which is the subject of this Proclamation.

፪/ በሠራተኛነቱ ወይም ባለው የሥራ ቦታ በምርት ግብይት ውሎች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ወይም ተፅዕኖ የማድረግ አዝማሚያ ያለው በሕዝብ ያልታወቀ መረጃን ማግኘት የሚችል ማንኛውም የባለሥልጣኑ የቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም ተወካይ ሆነ ብሎ በምርት ገበያ ውስጥም ሆነ ውጭ በሚደረግ ግብይት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲሳተፍ ለማስቻል ያገኘውን መረጃ ለሌላ ሰው ካቀበለ ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተውን መረጃ ከማንኛውም የባለሥልጣኑ የቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም ተወካይ የተቀበለ ወይም የወሰደና መረጃውን በምርት ገበያ ውስጥ ወይም ከምርት ገበያ ውጭ ለሚካሄድ ግብይት የተጠቀመ ማንኛውም ሰው ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

## ፳፱. <u>የባለሥልጣኑን መመሪያ ስለመጣስ</u>

የማናቸውም የምርት ገበያ ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ወይም የግብይት ፈጻሚዎች ማኅበር ሠራተኛ፣ የአስተዳደር ቦርድ አባል ወይም አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የወጡትን መመሪያዎች በራሱ ፈቃድ ሆነ ብሎ በመጣስ፣

፩/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ወይም በሌላ ሰው ስም በምርት ግብይት ውል ከተገበያየ፣

፪/ በሠራተኛነቱ ወይም በአባልነቱ ከሥራው ጋር በተያያዘ ያገኘውን ለሕዝብ ያልተገለጸ መረጃ ከሥራው አፈጻጸም ጋር በማይጣጣም ሁኔታ ለማናቸውም ዓላማ እንዲታወቅ ካደረገ፣

፫/ መረጃው የዚህን አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌን በመጣስ ከምርት ገበያ ወይም ከክፍያ ፈጻሚዎች ማኅበር ሠራተኛ፣ የአስተዳደር ቦርድ አባል ወይም አባል የተገኘ መሆኑን እያወቀ ይህንኑ መረጃ መሠረት በማድረግ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ወይም በሌላ ሰው ስም በምርት ግበይት ውል ከተገበያየ፣ ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

2/ It shall be a criminal offense punishable by a fine of at least Birr 20,000 and not more than Birr 100,000 and imprisonment for not more than five years for any Board Member of the Authority or any employee or agent thereof, who by virtue of his employment or position, acquires information which may affect or tend to affect the price of any Exchange traded contract for which such information has not been made public, to impart such information with intent to assist another person, directly or indirectly, to participate in any Exchange or off-Exchange transaction.

3/ It shall be a criminal offense punishable by a fine of not more than Birr 20,000 and not more than Birr 100,000 and imprisonment for not more than five years for any person to acquire such information as described under Sub-Article(2) of this Article from any Board member of the Authority or any employee or agent thereof and to use such information in any Exchange or off-Exchange transaction.

## 29. Violations of Directives of the Authority

It shall be a criminal offense punishable by a fine of at least Birr 20,000 and not more than Birr 1000,000 and imprisonment for not more than five years for any person who is an employee, member of the governing board, or member of any committee of a Commodity Exchange, Clearing Institution, or Exchange Actors Association, in violation of a directive issued by the authority, willfully and knowingly, to:

1/ trade for such person's own account, or for or on behalf of any other account, in Exchange traded contracts

2/ disclose for any purpose inconsistent with the performance of such person's official duties as an employee or member, any significant non-public information obtained through special access related to the performance of such duties;

3/ trade for such person's own account, or for or on behalf of any other account, in Exchange traded contracts on the basis of any significant non-public information that such person knows was obtained in violation of Sub-Article(2) of this Article from an employee, member of the governing board, or member of any committee of a recognized Exchange, Clearing Institution, or Exchange Actors Association.

## ክፍል ሰባት
## የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ

### ፴. ስለዋስትና ፈንዱ መቋቋምና አጠቃቀም

፩/ የምርት ገበያ የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ያቋቁማል።
ፈንዱም፣

ሀ/ ለክፍያና ርክክብ ማስፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ወጪዎችና ጥበቃ ማቻቻያ ወይም መደጎሚያ፣

ለ/ በምርት ገበያ የውስጥ ደንቦች መሠረት ከተከናወነ የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም ለሚያጋጥሙ ጉድለቶች በጊዜያዊ ማሚያነት ለመጠቀሚያ፣

ሐ/ እንደ አስፈላጊነቱ ለምርት ገበያ የኢንሹራንስ አረቦን ክፍያ ለመፈጸም፣ እና

መ/ በባለሥልጣኑ ለሚወሰን ሌሎች የባለሥልጣኑ አግባብ ያላቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች ማስፈፀሚያ ሊውል ይችላል።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ዓላማ የምርት ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርት ገበያን የክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድን የሚያስተዳድር የሥራ አመራር ንዑስ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል።

### ፴፩. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ባለሥልጣኑ፣

፩/ ስለክፍያና ርክክብ ፈንድ መዋጮ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ፣

፪/ ስለክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር፣

፫/ ስለገንዘብ አወጣጥና ስለመልሶ ክፍያ፣

፬/ ስለሽፋንና ከሽፋን ውጭ ስለመሆን፣

፭/ ስለአገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያዎች፣ እና

፮/ ግዴታን ባለመፈጸም ስለሚጣሉ ቅጣቶችና የዲሲፕሊን እርምጃዎች፣
መመሪያ ያወጣል።

## PART SEVEN
## SETTLEMENT GUARANTEE FUND

### 30. Utilization of Settlement Guarantee Fund

1/ A Commodity Exchange shall set up a Settlement Guarantee Fund that may be applied for:

a) offsetting the expenses and maintenance of the Settlement Guarantee Fund;

b) temporary application to meet shortfalls and deficiencies arising out of the Clearing and Settlement obligations of the Clearing Institutions carried out in accordance with the by laws and rules of a Commodity Exchange;

c) payment of premium on insurance coverage by a Commodity Exchange, if any; and

d) any other purpose as may be specified by the Authority.

2/ For the purposes of Sub-Article(1) of this Article, the Board of Directors of a Commodity Exchange may, by resolution, appoint a management subcommittee to administer the Settlement Guarantee Fund of A Commodity Exchange.

### 31. Power to issue Directives

The Authority shall by directives pursuant to this Proclamation determine:

1/ mode and amount of contributions to the Settlement Guarantee Fund;

2/ administration of the Settlement Guarantee Fund;

3/ conditions of withdrawal and repayment;

4/ coverage and exclusion;

5/ charges for utilization: and

6/ penalties and disciplinary actions for non-performance.

## ክፍል ስምንት
## የአስቸኳይ ሁኔታ ሥልጣን

### ፴፪. የባለሥልጣኑ ሥልጣን

ባለሥልጣኑ አስቸኳይ ሁኔታ ተከስቷል ብሎ ሲያምን የምርት ግብይት ሥርዓቱን ለመጠበቅ ወይም ለማስተካከል በተለይ የሚከተሉትን እርምጃዎች የምርት ገበያው እንዲወስድ መመሪያ መስጠት ይችላል፣

፩/ ማናቸውም የግብይት ውልን የመሰረዝ፣

፪/ በማናቸውም የግብይት ውል ላይ ጊዜያዊ እገዳ የመጣል፣

፫/ በማናቸውም የግብይት ውል ላይ ጊዜያዊ የአስቸኳይ የማያዣ መጠን የመወሰን፣ እና

፬/ የባለሥልጣኑ ውሳኔ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በቅን ልቦና በተገኘ የገበያ አቋም ላይ የሚደረገውን ገደብ የመወሰን።

### ፴፫. አቤቱታ

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱ ለአቤት ባዩና ለባለሥልጣኑ ማስታወቂያ እንዲደርሳቸውና እንዲሰሙ ካደረገ በኋላ የባለሥልጣኑ ውሳኔ በዘፈቀደ የተሰጠ፣ በማስረጃ ያልተደገፈ ወይም ሕግን ያልተከተለ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር የባለሥልጣኑን ውሳኔ ማገድ አይችልም።

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፬. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስ ፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል።

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

## PART EIGHT
## EMERGENCY POWERS

### 32. Power of the Authority

When the Authority has reason to believe that an emergency exists, it may direct a Commodity Exchange to take action which is necessary to maintain or restore orderly trading, including but not limited to:

1/ liquidation of any contracts;

2/ temporary suspension of trading on any contract;

3/ setting of temporary emergency margin levels on any contract; and

4/ fixing limits that may apply to a market position acquired in good faith prior to the effective date of the Authority's action.

### 33. Appeal

any party adversely affected by the decision of the Authority under Article 32 of this Proclamation may petition the Federal High Court. The Court shall base its decision upon an examination of all the information before the Authority at the time the determination was made. The court shall not enter an injunction unless it has determined, after notice and hearing before the court, that the Authority action complained of was arbitrary, not supported by the weight of evidence or established rules of law, an abuse of discretion, or otherwise not in accordance with law.

## PART NINE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 34. Power to issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Authority shall issue directives necessary for the proper implementation of this Proclamation.

## ፴፭. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

## ፴፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 35. Inapplicable Laws

No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters covered under this Proclamation.

## 36. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of September, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**